National Institute for Public Health
and the Environment
*Ministry of Health, Welfare and Sport*

# ሳንባ ነቀርሳ ምንድን ነው?



# ሳንባ ነቀርሳ ምንድን ነው?

ሳንባ ነቀርሳ (tbc) በባክቴሪያ የሚመጣ ኢንፌክሽን በሽታ ነው። ሳንባ ነቀርሳ አብዛኛውን ጊዜ በሳንባ ውስጥ ይከሰታል። ሆኖም ግን፣ በሌሎች የሰውነት ክፍሎችም ሊገኝ ይችላል። ሳንባ ነቀርሳ አብዛኛውን ጊዜ በመድኃኒት በሚገባ ሊታከም ይችላል። ሳንባ ነቀርሳ በኔዘርላንድ እምብዛም አይታይም።

# ሳንባ ነቀርሳ መኖሩን እንዴት መለየት እችላለሁ?

ሳንባ ነቀርሳ የሚከሰተው በባክቴሪያ ነው። በሽታው፣ ባክቴሪያው ወደ ሰውነት ከገባ በኋላ በኋላ ከወራት ወይም ከዓመታት በኋላ ሊከሰት ይችላል። ባክቴሪያውን የያዛቸው ሰዎች ሁሉ ይታመማሉ ማለት አይደለም። የሚታመሙ ሰዎች በሳንባቸው ወይም በሌላ የሰውነት ክፍል ሳንባ ነቀርሳ ይኖራቸዋል። ለምሳሌ፣ በአጥንቶች፣ በሊምፍ እጢዎች ወይም በአከርካሪ አጥንት ውስጥ ሊሆን ይችላል። ሳንባ ነቀርሳ ያለባቸው ሰዎች የሚከተሉትን ምልክቶች ሊታዩባቸው ይችላሉ፡

## በብዛት የሚያጋጥሙ ምልክቶች


ከሶስት ሳምንታት በላይ የሚቆይ ሳል


መቢስሉበት ጊዜ አክታ ወይም ደም መኖር


በሌሊት በጣም ማላብ


የሰውነት ክብደት መቀነስ


የምግብ ፍላጎት ማጣት


ድካም

ሌሎች ምልክቶች የሚከተሉት ናቸው፡
- ትኩሳት
- የመተንፈስ ችግር
- የደረት ህመም
- የእጢዎች እብጠት (የሳንባ ነቀርሳ ባክቴርያ በእጢዎች በሚኖርበት ጊዜ)
- ህመም፣ እብጠት (የሳንባ ነቀርሳ ባክቴርያ በአጥንት በሚኖርበት ጊዜ)

# የሳንባ ነቀርሳ እንዳለብኝ እንዴት አውቃለሁ?

ከሳንባ ነቀርሳ ጋር የሚያያዙ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ምልክቶች በራስዎ ላይ ያስተውላሉ? እንደዛ ከሆነ ወደ የቤተሰብ ሐኪምዎ ይደውሉ። ሐኪምዎ ወደ ሌላ ሐኪም ሊልክዎት ይችላል።

- ኤክስሬይ ወይም ስካን
- ከሳንባ የሚወጣውን አክታ መመርመር
- ከሳንባ ውጭ በሳንባ ነቀርሳ የመያዝ አደጋ ካለዎት የሚደረጉ ሌሎች ምርመራዎች

# በሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን እና በሳንባ ነቀርሳ በሽታ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

**የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን**
አንድ ሰው በሳንባ ነቀርሳ ባክቴሪያ ተበክሏል፣ ግን ደግሞ አልታመመም? ስለዚህ ይህ የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ይባላል። የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ያለበት ሰው በሽታው ለሌሎች ተላላፊ አይደለም።

ይህ በራሪ ጽሑፍ ስለ ሳንባ ነቀርሳ በሽታ ነው። ስለ ሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ተጨማሪ መረጃ 'ሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን' (english) በሚለው በራሪ ጽሑፍ ውስጥ ይገኛል።

**የሳንባ ነቀርሳ በሽታ**
የሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን ካለባቸው ከአስር ሰዎች መካከል አንዱ በሳንባ ነቀርሳ በሽታ ይያዛል። ይህ ከጥቂት ወራት በኋላ ሊከሰት ይችላል፣ ነገር ግን ከዓመታት በኋላ ጭምር ሊከሰት ይችላል። አንድ ሰው በባክቴርያው ከተበከለ በኋላ የመታመም እድሉ በመጀመሪያዎቹ ሁለት ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ ነው።

**ሳንባ ነቀርሳ አብዛኛውን ጊዜ በሳንባዎች ይከሰታል።**
ይህ ተላላፊ ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን የግድ ተላላፊ ይሆናል ማለት አይደለም። አንድ ሰው በሳንባ ውስጥ የሳንባ ነቀርሳ ባክቴርያ አለበት? ስለዚህ ሐኪሙ ይህ ሰው ተላላፊ የሳንባ ነቀርሳ እንዳለበት ለማረጋገጥ ይመረምራል።

ሳንባ ነቀርሳ በአጥንት፣ በሊምፍ እጢዎች፣ በአከርካሪ አጥንት ወይም በሌሎች የሰውነት ክፍሎች ውስጥም ሊኖር ይችላል። በዚህ ሁኔታ ተላላፊ አይደለም።

## ሳንባ ነቀርሳ እንዴት ይይዘኛል?

በሽታውን ወደ ሌሎች ማስተላለፍ የሚችለው ተላላፊ የሳንባ ነቀርሳ ያለበት ሰው ብቻ ነው። በሚስሉበት፣ በሚያስነጥሱበት፣ በሚናገሩበት ወይም በሚዘፍኑበት ጊዜ የሳንባ ነቀርሳ ባክቴሪያ የያዙ ትናንሽ ጠብታዎች ወደ አየር ይሰራጫሉ። ሌሎች ሰዎች እነዚህን ጠብታዎች ወደ ውስጥ በመተንፈስ በባክቴሪያው ሊበከሉ ይችላሉ።

## ሳንባ ነቀርሳ በምን መንገዶች አይይዘኝም?

በሚከተሉት መንገዶች ሳንባ ነቀርሳ አይያዙም:

- እጅን በመጨባበጥ፣ በመተቃቀፍ ወይም በመሳሳም
- ምግብ እና መጠጦችን በመጋራት
- የሌላ ሰውን ኩባያ፣ ሳህኖች፣ ማንኪያና ሹካ፣ ልብሶች ወይም መጸዳጃ ቤት በመጠቀም
- በወሲባዊ ግንኙነት
- ከደም ጋር በሚኖር ንክኪ

## የምንጭ እና የንክኪ ምርመራ

GGD የሳንባ ነቀርሳ ያለባቸውን ሰዎች ይረዳል። አንዳንድ ጊዜ GGD ኢንፌክሽኑ ከየት እንደመጣ ለማወቅ ምርመራ ያካሂዳል። ይህ የምንጭ ምርመራ ይባላል። ተላላፊ የሳንባ ነቀርሳ ያለበት ሰው ሌሎችን ሊበክል ይችላል። ስለዚህህ GGD በዚያ ሰው አቅራቢያ ያሉ ሰዎችን ይመረምራል። ይህ የንክኪ ምርመራ ይባላል። የንክኪ ምርመራ ዓላማ በሳንባ ነቀርሳ ባክቴሪያ የተበከሉ ሰዎችን በተቻለ ፍጥነት ማግኘት እና ማከም ነው። እንዲህም እነዚህ ሰዎች በሽታውን እንዳይይዙ ይረዳል።

ስለ የምንጭ እና የንክኪ ምርመራ ተጨማሪ መረጃ፣ 'ሳንባ ነቀርሳ እና የምንጭ እና የንክኪ ምርመራ' (english) በሚለው በራሪ ጽሑፍ ውስጥ ይገኛል።

## ሳንባ ነቀርሳ ሊታከም ይችላል?

ሳንባ ነቀርሳ አብዛኛውን ጊዜ የተለያዩ መድሃኒቶችን በማቀናጀት በሚገባ ሊታከም ይችላል። ሕክምናው አብዛኛውን ጊዜ ስድስት ወራት ይወስዳል።

ስለ የሳንባ ነቀርሳ ሕክምና ተጨማሪ መረጃ 'ሳንባ ነቀርሳ እና እንዴት እናክመዋለን' በሚለው በራሪ ጽሑፍ ውስጥ ይገኛል።

## ተላላፊ የሳንባ ነቀርሳ በሚኖርበት ጊዜ የሚወሰዱ እርምጃዎች

አንድ ሰው ተላላፊ የሳንባ ነቀርሳ ካለበት፣ ያ ሰው ቢያንስ ለ2 ሳምንታት ከሌሎች ተለይቶ ይቆያል። ይህ ባክቴሪያው እንዳይሰራጭ ይከላከላል። ይህ ማግለል ይባላል።

ተላላፊ የሳንባ ነቀርሳ በሚኖርበት ጊዜ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች ተጨማሪ መረጃ፣ 'የሳንባ ነቀርሳ - ስርጭት፣ የሳል ንፅሕና እና የአኗኗር ዘይቤ መመሪያዎች' (english) በሚለው በራሪ ጽሑፍ ውስጥ ይገኛል።

## በሳንባ ነቀርሳ ኢንፌክሽን የመያዝ ዕድል ያለው ሰው ማን ነው?

አንዳንድ ሰዎች በሳንባ ነቀርሳ ባክቴሪያ የመያዝ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው:

- ተላላፊ የሳንባ ነቀርሳ ካለበት ሰው ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ የነበሩ ሰዎች።
- ሳንባ ነቀርሳ በብዛት በሚገኝበት አገር የተወለዱ ሰዎች።
- እንደ አፍሪካ፣ እስያ፣ ደቡብ አሜሪካ እና ምስራቅ አውሮፓ ያሉ የሳንባ ነቀርሳ በሽታ በብዛት ወደሚገኝባቸው አካባቢዎች የሚጓዙ ሰዎች።

## በሳንባ ነቀርሳ በሽታ የመያዝ ዕድል ያለው ሰው ማን ነው?

አንዳንድ ሰዎች በሳንባ ነቀርሳ በሽታ የመያዝ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው:

- ዕድሜያቸው ከ5 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት።
- በበሽታ ምክንያት፣ በሽታ የመከላከያል አቅማቸው ደካማ የሆኑ ሰዎች።
- በሽታ የመከላከል አቅምን የሚቀንሱ መድሀኒቶች የሚወስዱ ሰዎች።

## የሳንባ ነቀርሳ ክትባት መውሰድ የሚችለው ማን ነው?

በኔዘርላንድ፣ ሳንባ ነቀርሳ በብዛት በሚገኝበት አገር ከተወለዱ ወላጆች ለተወለዱ ሕፃናት፣ የሳንባ ነቀርሳ የ BCG ክትባት ይሰጣል። ሕፃናት ገና በለጋ እድሜያቸው ክትባቱን መውሰድ ይችላሉ። ክትባቱ ከሳንባ ነቀርሳ በሽታ 100% መከላከል አይሰጥም። ይሁን እንጂ፣ ከክትባት በኋላ እንደ ማጅራት ገትር ያሉ በጣም ከባድ የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ዓይነቶች የመያዝ ዕድል በጣም ዝቅተኛ ነው።

የ BCG ክትባት ለአዋቂዎች እንደ ሕፃናት ያህል መከላከል አይሰጥም። ስለዚህህ፣ ለተወሰኑ አዋቂዎች ብቻ ነው የ BCG ክትባት እንዲወስዱ የሚመከረው።

ስለዚህህ ተጨማሪ መረጃ 'የ BCG ክትባት' (english) እና 'ጉዞ እና ሳንባ ነቀርሳ' (english) በሚሉት በራሪ ጽሑፎች ውስጥ ይገኛል።

# ተጨማሪ መረጃ

- ስለ ሳንባ ነቀርሳ ተጨማሪ መረጃ በ rivm.nl/tuberculose ይገኛል።
- ስለ ሳንባ ነቀርሳ ጥያቄዎች አሉዎት? በአከባቢዎ የሚገኘውን የ GGD የሳንባ ነቀርሳ መቆጣጠር ክፍል ያነጋግሩ። የእርስዎን GGD በ ggd.nl በኩል ማግኘት ይችላሉ።

This information is available in English at:
Waxaad warbixintan ku aqrisan kartaa Soomaaliga:
Informacje te są dostępne w języku polskim na stronie:
ነዚ ሓበሬታ ብቋንቋ ትግርኛ ኣብዚ ዝስዕብ ከተንብብ ትኽእል ኢኻ፡
ይህንን መረጃ አማርኛ በሚከተለው ማንበብ ይችላሉ፡

شما میتوانید این معلومات را به  دریاز طریق ذیل مطالعه کنید:
يمكنك قراءة هذه المعلومات باللغة العربية على:

www.rivm.nl/en/tuberculosis/
information-materials#aboutTB

ጥያቄዎን ለቲቢ ቻት-ቦት (TBC-chatbot) ያቅርቡ፡
www.tuberculose.nl/over-tuberculose

Published by

**National Institute for Public Health
and the Environment, RIVM**
P.O Box 85104 | 3508 AC  Utrecht
The Netherlands
www.rivm.nl/en

Oktober 2026

Committed to health
and sustainability

016979_AM